# ፋሲካን በመንገድ ዳር

## ከሞረሽ ወገኔ የባህል ማህበር በስዊድን

ፋሲካ ክርስቶስ ከሞት የተነሳበት በመሆኑ፣ በተለይ ሁለት ወር ጾሞ፣ ሁለትና ሶስት ቀን አክፍሎ ለሚፈስክ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክሳዊት ተዋህዶ ቤተክርስቲያን ተከታይ ለሆኑ ክርስቲያኖች ትልቅ በዓል ነው። ይሁን እንጂ የትግራይ ብሂረተኞች በኢትዮጵያ ስልጣን ከያዙ ጊዜ ጀምሮ በተከታታይ አማራውን ህዝብ በእቅድ በፋሲካ ከቤቱ ያባርሩታል፣ ከኖረበት ያፈናቅሉታል፣ ያስሩታል፣ ይገሉታል።

የዚህ የያዝነውን አመት የትንሳኤ ባእል የወሎና የላሊበላ አካባቢ ህዝብ ተርቦ፣ ትግራይ ተትረፍርፏት፣ የወሎና የላሊበላ ሰዎች "ጸጉረ ልውጥ" ተብለው ትግራይን ለቀው እንዲወጡ ሆነዋል።

በባህር ዳር የከተማው አስተዳደር የመኖሪያ ቤቶችን በግሬደር እያፈረሱ የሰው ነፍስ ሳይቀር ጠፍቶ ከ200 በላይ ሰዎች ታስረዋል። የተራቡትም ሆነ ቤታቸው የሚፈርስባቸው ዜጎች ፋሲካቸው ምን ሊመስል እንደሚችል ለብሂረተኞችም፣ ለወያኔዎችም ሆነ ለኢትዮጵያኖች ለህሌናቸው ፍርድ እንተወው።

የትንሳኤ በዓል በቀረበና በመጣ ቁጥር በአማራው ህዝብ ላይ የሚደርሰው ከቤቱ መባረር፣ ከኖረበት አካባቢ መፈናቀል ወይም መታሰርና መሰደድ እንግዳ አይደለም።

የትግራይ ብሂረተኞች ስልጣን ይዘው አዲስ አበባን ከተቆጣጠሩ በሁዋላ በአቶ ሰዬ አብርሃ መሪነትና አዛዥነት የኢትዮጵያን ወታደር "የአማራ ወታደር ነው" በማለት የፋሲካ ቀን ጥዋት ከቤታቸው በመሳሪያ አባረው እቃና ልብሳቸውን መንገድ አውጠው እንደጣሉባቸው አይረሳም። ትግሬዎች የኢትዮጵያ ተዋህዶ ኦርቶዶክሳዊት ቤተክርስቲያን አማኞች በመሆናቸው የፋሲካን በዓል ትልቅነት በጥልቅ ስለሚያውቁ በዚህ ድርጊታቸው ምን ያህል በአማራው ህዝብ ላይ ያላቸውን ጥላቻ ልብ ይበሉ።

ሚያዚያ 8/2004 ዓም በፋሲካ ሌሊት በጉራ ፈረዳ 3000 የአማራ ተወላጆች ተፈናቅለው ሰባት ቤቶች በካድሬዎች መቃጠሉን ካድሬዎች ከማመን አልፈው የወረዳው ባለስልጣኖች መጋቢት 29/2004 የአማራ ተወላጅ የሆኑትን በአዳራሽ ሰብስበው "እስካሁን ከአካባቢያችን ያስወጣነው 3000 ሰዎችን ብቻ ነው። በእቅዳችን መሰረት 22000 እናስወጣለን ...." ብለው በጦር እየወጉ፣ ቤት ንብረታቸውን እያቃጠሉ፣ አራሶችን ከአልጋ አንስተው ዉጭ እየጣሉ ... ከሀገር ማፈናቀላቸውን አንርሳ።

ትዝታችሁን ወደሁዋላ እንውሰደውና፣ በጎጃም ተራ ገበሬዎች "ቢሮክራቶች" ተብለው ከሚያርሱበት ቦታ ተነቅለው ለአቤቱታ ወደ አዲስ አበባ ሲሄዱ ብዙዎቹ በበርሀ አልቀዋል። እንዲሁም አሁን ድረስ በጎንደር ያሉ ገበሬዎች እንደ ጎጃም ገበሬዎች "ቢሮክራቶች" ተብለው መሬታቸውን አይነጠቁ እንጂ፣ ለኢንቬስተሮች ልቀቁ እየተባሉ መሬታቸውን ለትግራይ አዲስ መኳንቶች እየለቀቁ መንገድ ዳር አዳሪ እየሆኑ ናቸው፤ የወያኔ መንግስት ጎንደር ለምቷል ብሎ ለሚያቀርበው ፕሮፖጋንዳ፣ ያውም የትግራይ ተወላጁ የሆኑት ኩሩው ኢትዮጵያዊ አቶ ጌታቸው ረዳ ብሎግ ገብተው በትግራይና በጎንደር መካከል ያለውን የልማት ልዩነት ይመልከቱ። http://ethiopiansemay.blogspot.se በዚህ ጽሁፍ ስለጎንደር ስንጠቅስ፣ አንድ የአማራ ዘር ጠፍቶ በትግራይ ሰዎች የተተካበትን የወልቃይትን አካባቢ ሳንጨምር ነው።

ሰሞኑን በአውስትራሊያ ከሚኖሩ የወልቃይት ሰዎች ጋር አቶ ታማኝ ባደረገው ቃለመጠይቅ እንደተረዳነው፣ በወልቃይት የአማራን ዘር በማጥፋት ዘመቻ ሴት ወንድ፣ ህጻን ሽማግሌ ሳይል ታስረው ባለቁበት እስር ቤት ተርፈው የወጡ ሁለት ሰዎች ብቻ መሆናቸውን ነው። በተጨማሪም የኢሳት ቴሌቪዥንን ከሁለት የወልቃይት ሰዎች ጋር ያደረገውን ረዥም ቃለመጠይቅ ይመልከቱ። በዚያ እስር ቤት ውስጥ በብዙ ሺዎች የሚቆጠሩ የወልቃይት ሰዎች ገብተው በምን አይነት ሁኔታ እንዳለቁ የሚታወቅ መረጃ የለንም። የይሁዳውያንን በአሽዊዝ እስርቤት በጀርመን ናዚዎች እልቂት ሳንወድ አንበን እንድናነጻጽር ያስገድደናል።

በአዲስ አበባ የአማራው ህዝብ በእስር ቤቶች ስለሚደርስበት የመንፈስና የአካል ሰቆቃ ዶክተር አሰፋ ነጋሽ ተርጉመው ያስነበቡንን ወደሁዋላ ሄደው ያንቡ። ግን ከዚህ ሌላ ካድሬ ያልጻፈለት፣ የወያኔ ሰዎች የማይናገሩት በየክልሉና በየከተማው በአማራነታቸው ብቻ ተወንጅለው አማሮች እስር ቤቱን ማጠበባቸውን ነው። ፍኖተ ነጻነት ጋዜጣ ግንቦት 4/2004 ባወጣው እትሙ "መታወቂያቸው አማራ ስለሚል ብቻ ታሰሩ" ይላል። ሌላም ብዙ መጥቀስ እንችላለን።

የትግራይ ብሂረተኞች ስልጣን ከያዙ ጊዜ ጀምሮ አንድ ሰው አማራ መሆኑ ብቻ ወንጀል ሆኖበት መታሰሩ፣ መፈናቀሉ፣ የሁዋሊት ታስሮ በገደል መጣሉ፣ መገደሉ ወዘተ 23 ዓመት ሳያቋርጥ በየቀኑ የምንሰማው መሆኑ ብቻ አይደለም የትግል መንፈሳችንን የቀሰቀሰው፤ ከዚያ አልፎ አማራ ገድለህል ተብሎ ለፍርድ የቀረበ አንድም ሰው አለመኖሩ፣ ሌላው ቀርቶ ኢትዮጵያዊ ነኝ እያሉ የሚሳለቁትን ሳይቀር አለማነጋገሩ "በእንቅርት ላይ ጆሮ ደግፍ" እንደሚሉት ሆኖ፣ ትግላችን ቆራጥነት እንደሚጠይቅ አስተምሮናል። አማሮች ወንጀላቸው አማራ መሆናቸው ብቻ ሆኖ ቤት ተዘግቶባቸው ተቃጥለዋል፣ በገደል ተጥለዋል፣ እርጉዝ ሴት ሆዷ ተቀዶ ሽል እንድታይ ሆናለች፣ በጣም ብዙ ለመስማት የሚቀፉ ወንጀሎች በዚህ ህዝብ ላይ ተፈጽሟል። ነገር ግን በአማራው ህዝብ ላይ እንዲህ አይነት ወንጀል የፈጸሙ ሰዎች ለፍርድ ከመቅረብ ይልቅ በተቃራኒው የአማራውን ህዝብ በማፈናቀላቸው፣ በመግደልና በማስገደላቸው ሹመትና ክብር ሲያገኙ አይተናል፣ በምሳሌነት አቶ ሰዬ አብርሀምን፣ አቶ ታምራት ላይኔን፣  አቶ ሽፈራው ሽጉጤን ወዘተ መጥቀስ ይቻላል። ይህ ደግሞ በሀገር ውስጥና ከሀገር ውጭ ስልጣን አንጋጣጮችንና ጥቅም ናፋቂዎችን ፈልፍሎ በአማራው ሕዝብ ላይ የሚፈጸመውን የዘር ማጥፋት ዘመቻ እንዲነገር እንኳ የማይፈልጎ ከሊቅ እስከ ደቂቅ መኖራቸውን አስተውለናል፡፡

የአማራ ክልል ተብሎ በተከለለው ለአቅመአዳም የደረሱ ሴቶች እንዳይወልዱ ማምከኛ መድህኒት እንዲወጉ ሆኖዋል፤ በክትባት መልክ የኤድስ በሽታ በህዝብ መካከል እንዲዛመት ተደርጓል።

በኢትዮጵያ ከአማራው ህዝብ ወገን የሆነ ማነኛውም ወጣት የከፍተኛ ትምህርት እድል እንዳያገኝ በአቅም ግንባታ ሚኒስቴሩ በአቶ ተፈራ ዋልዋ በመንግስት ደረጃ በህግ ታግዶ ለዘመናት አማራው የከፍተኛ ትምህርት እድል እንዳያገኝ ተከልክሎ ይገኛል። ከ500 000 በላይ የትግራይ ሰዎች አዲስ በሰፈሩበት የወልቃይት አካባቢ፣ ባካባቢው በህይወት የቀሩ የአማራ ተወላጆች 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት እንዳይገቡ መከልከላቸውን ወልቃይት የሚለው ድህረገጽ በኦክቶበር 2/ 2013 ዘግቧል።

"ጨው ለራስህ ብለህ ጣፍጥ" ይባላል። የቀድሞው የቀሓሥ ዩኒቨርሰቲ ያሁኑ የኦነግ ሊቅ አቶ ኢፕሳ ጉተማ "ዘ ፕሪዝነር ኦፍ ኮንሽየስ"፣ በሚለው መጽሀፉ "ኢትዮጵያ የሚሉ አማሮች ብቻ ናቸው፣ እነሱ ደግሞ እርስ በርሳቸው ስለማይስማሙ አንድ ቦታ ከቦ እንዲጠፉ ማድረግ ነው" ይላል። የትግራይ ነጻ አውጭ ግንባር ከስልጣን በፊት የነበሩ ጽሁፎችም ሲነበቡ በአማራነትና በኢትዮጵያዊነት መካከል ያለው ልዩነት የጸጉር ስንጠቃ ካልሆነ በቀር ብዙ ጊዜ ቦታ

ይቀያየራሉ። ትናት የነበረውን ዛሬ እንርሳው ካላልን በቀር የትግራይ ብሄረተኞች "ኢትዮጵያ የምትባል ሀገር የለችም፣ አማራ የፈጠራት ናት" ማለታቸውን አንርሳ። ፈጣሪው ከጠፋ ተፈጣሪው ጸንቶ አይኖርምና ስለዚህ ኢትዮጵያ የምትባል ሀገር እንዳትጠፋ እንቅፋት የሚሆነው አማራው ነው ብለው ወስነዋል። ምንም እንኳ በታሪክ የተመዘገበ ኢትዮጵያኖች ሀገራቸውን "አቢሲኒያ" ብለው የጠሩበት ጊዜ ባይኖርም፣ የኦነጎች ኢትዮጵያን አቢሲኒያ እያሉ መጥራት ኢትዮጵያን እንደሀገር የማጥፋት ሴራው አንዱ ተልእኮ ነው።

የሞረሽ ወገኔ የባህል ማህበር በስዊድን በሀገር ውስጥና ከሀገር ውጭ የብሄር አክራሪ ሆነው አማራውን በጠላትነት ወንጅለው የሚያጠቁት ኢትዮጵያን ለማጥፋት ካላቸው ተልኮ ነው ብሎ ያምናል። አማራው ህዝብ እየተከሰሰ ያለው በኢትዮጵያዊነት አቀንቃኝነት መሆኑን አንርሳ። በህዝብ ልብ የኢትዮጵያዊነት እምነት ከሌለ ጸንቶ የሚቆም ኢትዮጵያ የሚባል ሀገር አይኖርም። ኢትዮጵያ እንድትኖር ኢትዮጵያዊ ነኝ ብሎ የሚያምን ህዝብ መኖር አለበት። የአማራው ህዝብ የኢትዮጵያዊነቱን እምነት አውልቆ ጥሎ እንደሌሎች ብሔረተኞች ብሄረተኛ ካልሆነ እንደ ወልቃይት ህዝብ ይጠፋል፣ ካልሆነም በህይወት መኖር የሚፈልገውም ከስቃይ፣ ከስር፣ ከመፈናቀል ወዘተ ብዛት ኢትዮጵያዊነቱን አውልቆ ይጥላል በሚል ስሌት ከአማራው ህዝብ ኢትዮጵያዊነትን አጥፍቶ ኢትዮጵያ የምትባል ሀገር ከዐለም ካርታ ለመደለዝ፣ ዛሬ ኢትዮጵያዊ ነኝ ብሎ የሚያምነውን የአማራውን ህዝብ ቁጥር አንድ ተቀዳሚ ጠላታቸው አድርገው ከላይ ከጠቀስናቸው በብዙ እጥፍ የበዙ በደሎች ፈጽመውበታል። "ጨው ለራስህ ብትል ጣም" እንደሚባለው፣ አማራው እራሱን አድኖ ኢትዮጵያን ለመታደግ ያለ ምንም ማመንታት ተደራጅቶ ራሱንና ሀገሩን ማዳን አማራጭ የሌለው ብቸኛ መፍትሄ ነው ብለን እናምናለን። ኢትዮጵያዊነት ሲከፋም ሲደላም፣ በችግርም በደስታም ጊዜ እስከሞት ድረስ ከራስ ጋር የተገባ ቃልኪዳን ነው። ኢትዮጵያዊነት፣ አባት፣ አያት ቅድመ አያቶቻችን ከውስጥ ከሀዲና ከውጭ ወራሪ ሀገርን ለመጠበቅ ሲወድቁ በአደራ ያስረከቡን የአደራ ገንዘባችን ነው። አማራው ተደራጅቶ እራሱን ማስጠበቅ የለበትም ብለው የሚተቹ አንዳንድ ኢትዮጵያኖች፣ ኢትዮጵያዊነትን ከአማራው ህዝብ ገፈው በአማራጭ አዲስ የተፈበረከ ኢትዮጵያዊነት እንኳ ማቅረብ ያልቻሉ፣ የኢትዮጵያዊነት መስፈርታቸው በሀገርና በህዝብ መከፋፈልና በዘረኝነት ላይ የሀሳባቸውንና የእምነታቸውን መሰረት የገነቡ ከመሆን ያለፉ ሆኖ አይታይም። እንዲሁም የአንዳንዶቹ ኢትዮጵያዊነት "ባጣ ቆይኝ" አይነት ከመሆን ያለፈ ሆኖ ኢትዮጵያን በአንድ ሀገርና ህዝብነት የሚገነባ ሚዛን የደፋ ሀሳብ ሲያስተናገዱ አይስተዋሉም። የአማራው ህዝብ በኢትዮጵያዊነቱ ጸንቶና ኮርቶ እስከ መጨረሻው ትግሉን ይቀጥላል። ኢትዮጵያዊነት የነበረ፣ ያለና የሚኖር፣ የኢትዮጵያዊነታችንም ቅመሙ በ5ሺ ዘመን ታሪካችን በአባቶቻችን ደምና አጥንት የተገነባ ከእንቁ አልማዝ የከበረ እንቁ ነው።

ኢትዮጵያ በልጆቿ ጽኑና ቆራጥ የኢትዮጵያዊነት መንፈስ ተመልሳ በእግሯ ትቆማለች

ኢትዮጵያ በነጻነቷና በአንድነቷ ለዘላለም ኮርታ ትኑር

ይህ ጽሁፍ የሞረሽ ወገኔን የባህል ማህበር በስዊድን እምነት ያንጸባርቃል።

moweswe@gmail.com